# ሳታማኽኝ ብላ!!

ጠቢቡ በጥበብ መጽሐፍ ላይ “ሰው ሳይወድቅ በፊት ልቡ ከፍ ከፍ ይላል” እንዲል (ምሳሌ 18፥12) በአፍ፣ በዓይን፣ በእጅ፣ በእግር፣ በልብ ተሽለክልኮ በመግባት ስለሚወጋ አደገኛ ጦር እንዲሁም ደግሞ በዚህ ጦር ተወግተው ክፉኛ ስለቆሳሰሉ ትናንት <u>እውነትን በውሸት</u>፣ <u>ፍቅርን በጥላቻ</u>፣ <u>ሰላምን በሁከት</u>፣ <u>በረከትን በመርገም</u>፣ በመሸጥ ሰውን የበደሉ ዛሬ ደግሞ <u>ጽድቅን በኃጢያት</u>፣ <u>እምነትን በክህደት</u> <u>አንድ አምላክን በጣዖት</u> በመለወጥ አደባባይ ላይ የወጡ ከገዳያቸው ጋር “አንለያይም!” በማለት በፍቅር ስለወደቁ ሁለት ፍቅረኛሞች እናወጋለን።

ላለፉት ሁለት ሳምንታት ትልቅ መወያያ ርዕስ ሆኖ ሰንብተዋል “ምን ትላለህ” ቀዳሚ የምእመናን ጥያቄ ነበር እኔም በበኩሌ ሰሚ ጆሮ ከተገኘ እንዴት አይኖረኝም በማለት “አባ” ሆይ! በሥምዎ ሐወልትስ ሰርተዋል መርከብ ነው የቀሮት ወደብ ግን የሎትም” ብዬ ተቀኝቼ እንደ ነበር ይታወቃል። አሁን ደግሞ “ይብራራልን!” ባይ ቁጥር ከዕለት ወደ ቁጥሩ በርከት እያለ መጥተዋልና “አፍ” ያለው የሚመስል ግን የማይናገር፣ “ዓይን” ያለው የሚመስል የማያይ፣ “ጆሮ” ያለው የሚመስል የማይሰማ፣ “እጅና እግር ያለው የሚመስል” ዳሩ ግን የማይንቀሳቀስ ድዳ፣ ዕውር፣ ደንቆሮና ቆማጣ አራት ኪሎ በሚገኘው የተንጣለለ ፓላስ መቀመጫቸው ያደረጉ “አባ” ጳውሎስ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ምድር ያላቸውን ደንታቢስናት የሚገልጽ እውነተኛ ተምሳሌታቸው ሐምሌ አራት ቀን 2002 ዓ.ም በቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስተያን ቅጽር ግቢ አቆመዋል ለምን? አብረን የምናየው ይሆናል።

እንደው “አባ” ጳውሎስ አግኝቼ የመጠየቅ ዕድሉ ቢያጋጥመኝ ብዙ ነገርን ሳላበዛባቸው የማነሳቸው ጥያቄዎች ቢኖሩ 1ኛ. በምስልዎና በሥምዎ ተቀርጾ ስለ ቆመው ሐወልት ምን ይላሉ? የሚል ይሆን ነበር ቀዳሚ ጥያቄ። በመቀጠል ደግሞ እንደው እንደ አንድ በሐዲስ ኪዳን ላይ የተመሰረተችው (ያለቸውን) ቤ/ያን የኃይማኖት መሪ ሃሳቡ የእርስዎ ሃሳብ ከሆነ (ሐወልት እንዲቆምሎት ማለት ነው) መጽሐፍ ቅዱስ ይደግፈኛል ይላሉ? በምስልዎና በስምዎ ሐወልት ማስቆምዎ ግቡስ ምንድነው? ለአማንያን የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድ ነው? መቼም አንድን ነገር ግብ ሳይኖረው የሚሰራ ስራ አይኖርምና የእርስዎ ሐወልት በቤ/ን መካከል ማቆም ማለት ምን ማለት ነው? ትርጉሙ ምንድ ነው? “ማንኛውንም ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉ” እንዲል የእርሶ በምስልዎና በስምዎ ሐወልት ማቆም እንዴት ነው እግዚአብሔር የሚከብረው? ሃሳቡ የእኔ አይደለም ያሉ እንደሆነም- በቀረበሎት ፕሮግራም መሰረት ባለመስማማትዎ (ሐወልት በቤ/ን መካከል እንዲቆሙሎት) በህይወትዎም ሆነ በስልጣንዎ ሊያስከትልብኝ ይችላል የሚሉት አደጋ ምን ሊሆን ይችላል ብለው ይገምታሉ? የሚል ነበር። /“አባ” ጳውሎስ አግኝታችሁ የመጠይቅ ዕድሉ ያላችሁ ጋዜጠኞችም ሆናችሁ ግለሰቦች በዚህ አጋጣሚ ጥያቄን እንድታቀርቡልኝ በትህትና እጠይቃለሁ።/

ስለ ሁለቱ የሞት ጽዋ ማኅበር ፍቅረኛሞች ስለ ትዕቢትና “አባ” ጳውሎስ ለመግቢያ ያክል ጥቂት ልበልና በሰፊው ወደ ምንዳስሰው ዐብይ ርዕሰ ጉዳይ ማለት “የአባ” ጳውሎስ ድርጊት መነሻ ሃሳብ (ምንጩን) እና ውጤቱን አስመልክቼ ከምንም በላይ ደግሞ "ሐውልት ማቆም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው” መባሉም አያይዤ ጥቂት ማለት እፈልጋለሁ። ነገሩ እንዲህ ነው “አባ” ጳውሎስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ያን በአቦይ ስብሃት ደደቢታዊ ቡራኬ በሕገ-ወጥ መንገድ ከተሾሙ እነሆ ድፍን 18 ዓመታት አስቆጥረዋል። ጅብ ለአመሉ ... እንደሚሉት አበው በእነዚህ ዓመታት መካከል እኚህ ሰውዬ አንድም ቀን ቀና ብለው የሄዱበት ዕለት አለ ለማለት የሚደፍር ሰው ያለም አይመስለኝም። “አባ” ጳውሎስ በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ለቤተ-ክህነት ከሰሩት ሥራ ይልቅም “ለቤተ-መንግሥት” የዋሉትን ውለታ እጅግ ሚዛን እንደሚደፋም ዓለም ያወቀው ፀሐይ የሞቀው የአደባባይ ምሥጢር ነው። ሁላችን እንደምናውቀው የእኚህ “መኖክሴ” ስም በተነሳ ቁጥር በኢትዮጵያን ፊት የሚደቀነው ቤ/ያኒትዋ ኩፉኛ ያሸመደመዱ ክስተቶችና አሳፋሪ ታሪኮችም አሉ። “ሞኝና ወረቀት የያዙትን አይለቁም” እንዲሉ ከታሪክ መዛግብት በጥቂቱ የተመለከትን እንደ ሆነ፥

መጋቢት 27 ቀን 1985 ዓ/ም “አባ” ጳውሎስ በቀጨኔ መድኃኒአለም እንደ ውሻ በጫማ ተመተው የተባረሩበት ዕለት ሲሆን በ1985 ዓ/ም ደግሞ በዩናይትድ ስቴትስ ኦፍ አሜሪካ በባልቲሞር ውስጥ በገማ እንቁላል ተደብድበዋል። በጥር ወር 1991 ዓ/ም ደግሞ ጀርመን ሀገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ምዕመናን “አባ” ጳውሎስን ከቤ/ያን ያባረሩበትና የጀርመን ፖሊሶች ጣልቃ የገቡበት ጉዳይ ተጠቃሾች ናቸው። የግል ነገራቸው በተመለከተ ጠበቃዎቻቸው ፍራፍሬው ሲቀርባቸው ይጻፉት በማለት ትቼዋለሁ። እንግዲህ “አባ” ጳውሎስ በምስላቸውና በሥማቸው ሐወልት ሊያቆሙ ወደ ቻሉበት ምሥጢርና ምክኒያት ስንመጣ (<u>ወድ አንባቢ ሆይ! አሁን በዚህ ሰዓትና በዚህ ዓምድ ስለ ሐወልት ምንነትና አላስፈላጊነት ማተት የማዘናጋት ያህል ሆኖ ስለተሰማኝ አላደረግኩትም</u>) ይኸውም “አባ” ጳውሎስ ይቅር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት ሊኖረው ቀርቶ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ያን ወግ፣ ሕግ፣ ሥርዓትና ቀኖና ፈጽሞ የተወገዘና የተከለከለ በምድሪትዋ የ3000 ዓመት የክርስትና ታሪክም ያልታየና ያልተከሰተ እንግዳ ነገር ለመፈጸም (ለማድረግ) የሚያስችል ኃይል ሰጪ ንጥረ ነገር ከወዴት አገኙ? ማለት ነው ጥያቄ ሆኖ መነሳት የሚገባና ይህን ጥያቄ አብረን እንመልሰው።

“ንጉሥ ሆይ፥ ልዑል አምላክ ለአባትህ ለናቡከደነፆር መንግሥትንና ታላቅነትን ክብርንና ግርማን ሰጠው ስለ ሰጠው ታላቅነት ወገኖችና አሕዛብ በልዩ ልዩም ቋንቋ የሚናገሩ ሁሉ በፊቱ ይንቀጠቀጡና ይፈሩ ነበር የፈቀደውን ይገድል፥ የፈቀደውንም በሕይወት ያኖር ነበር የፈቀደውንም ያነሣ፥ የፈቀደውንም ያዋርድ ነበር። <u>ልቡ ግን በታበየ</u> <u>በኵራትም ያደርግ ዘንድ መንፈሱ በጠነከረ ጊዜ፥ ከመንግሥቱ ዙፋን ተዋረደ፥ ክብሩም ተለየው</u>። <u>ልዑል አምላክም በሰዎች መንግሥት ላይ እንዲሠለጥን</u>፥ <u>የሚወድደውንም እንዲሾምበት እስኪያውቅ ድረስ</u> ከሰው ልጆች ተይለቶ ተሰደደ፥ ልቡም እንደ አውሬ ልብ ሆነ፥ መኖሪያውም ከምድረ በዳ አህዮች ጋር ነበረ እንደ በሬ ሣር በላ፥ አካሉም በሰማይ ጠል ረሰረሰ።” እንዲል (ዳን. 5፥18-28)።

“አባ” ሆይ! እርስዎ የብዙ ሕዝብ መሪ፣ የኃይማኖት ሊቅና መጻህፍት አዋቂ ሳሉ ይህን ሁሉ እያወቁ በሰማይ ጌታ ላይ ኰሩ (አቅራሩ) እንጂ ልቦትን አላዋረዱም። በነቢያት፣ በሕግጋት፣ በሐዋርያትና በአበው ፈጽሞ የተከለከለና የተወገዘ ለራስዎ ክብር፣ ዝናና

ገናናነት ሐወልት አቆሙ፥ እርስዎና በዙሪያዎት የተኮለኮሉ ጆቢራዎች፣ መበለቶችና ወጠጢዎች ሰብስበው ልጆቹን ለማሳደግ ሲል ቁጭ በል ሲሉት ቁጭ የሚል ተነስ ሲሉትም የሚነሳ ቁም ሲባልም ያላንዳች ጥያቄ የሚቆሙሎትን ካህን ይዘው እያስጮኹና እያስዘመሩ ከከበረ ድንጋይ ከብረትም እንደ ወርቅም ከሚያብለጨልጭ ቅብ ያለ የተሠራ ሐወልት አቁሞው ውዳሴና ቅኔ ሲቀበሉና ሲሸምቱ ትንፋሽዎትንና መንገድዎትን ሁሉ በእጁ የያዘውን አምላክ ግን አላከበሩትም። ስለዚህም "አባ" ሆይ! እነዚህ የእጅ ጣቶች ከእርሱ ዘንድ ተልከዋል ይህም ጽሕፈት ተጽፎአል የተጻፈውም ጽሕፈት ማኔ ቴቄል ፋሬስ ይላል። የነገሩም ፍቺ ይህ ነው ማኔ ማለት፥ እግዚአብሔር ክህነትዎን (ሥልጣንዎት) ቈጠረው ፈጸመውም ማለት ነው። ቴቄል ማለት፥ በሚዛን ተመዘንህ፥ ቀልለህም ተገኘህ ማለት ነው። ፋሬስ ማለት፥ መንግሥትህ (ሥልጣን ክህነትህን) ተነሳ ተወሰደ ማለት ነው።" (አንባቢ ሆይ ያስተውሉ! አባ ጳውሎስ ምንም ከዚህ በኃላ መስቀል ይዘው በቤ/ያን ዓውደ ምህረት ላይ ቢወጡም ይህን ያስታውሱ ንጉሥ ሳዖል በእስራኤል ላይ የነገሠው ለ40 ዓመታት ቢሆንም ከእነዚህ ዓመታት መካከል ግን 37 ዓመት እግዚአብሔር የለበትም! ሳዖል በእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ንጉስ አይታወቅም ነበርና ተንቀህም መቀምጥ አለ)።

"አባ" ሆይ! ንጉሥ ናቡከደነፆር ክቡር የሆነ ፍጥረት ሳለ እንደ እንስሳ አጎንብሶ ሣር እስኪግጥ ድረስ ያደረገው አንድምታው ከልክ ያለፈ ትዕቢቱ ነበር። ይኸውም ዛሬ እርስዎ ለክብርዎ እንዳቆሙት ሐወልት በዳኒኤል መጽሐፍ ምዕ. 4፥30 ላይ "ንጉሡም ይህች እኔ በጉልበቴ ብርታት ለግርማዬ ክብር የመንግሥት መኖሪያ እንድትሆን ያሠራኋት ታላቂቱ ባቢሎን አይደለችምን? ብሎ ተናገረ" እንዲል። እንደው ናቡከደኖፆርማ እንደ እርስዎም መፃሕፍት ይደጉፉኛልም አላለልም ዛሬ እርስዎ ግን ፍፃሜ በሌላው ንቀትና ትዕቢት መጻህፍት ይደግፉኛል በማለት ሽብሽባዉን እና ዕልልታውን እየተቀበሉ ውሎዎትን ካሳለፉብ ቀን በምን ያንሳል ይበልጥ እንደሆነ እንጂ? መጽሐፍ እንደሚነግረን ሰይጣን ከመውደቁ በፊት በእግዚአብሔር ፊት የሚጋርድ ኪሩብ እንደ ነበረና በትዕቢት ተወጥሮ የራሱ ያልሆነውን እስካልተመኘ እና እስካልዳሰሰ ጊዜ ድረስም በመንገዱ ፍጽም እንደነበር ነው የሚነግረን።

ትዕቢት ልቡን አሳብጦ ዓይኑን ያሳወረው ዕለት ግን ነገሩ ተገለበጠና ይህን የንጋት ልጅ አጥቢያ ኮከብ እስኪባል ድረስ ከፍ ከፍ ብሎ የነበረውን ፍጥረት ከትዕቢቱ የተነሣ ከነበረበት ትልቅና የክብር ስፍራ ተወርውሮ ወደ ምድር ተጣለ። አዎ! ጠቢቡ በምሳሌው "ትዕቢት ጥፋትን ኵሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል" (ምሳሌ 16፥18) እንዳለው ሆነና እርስዎ ("አባ" ጳውሎስ) ደግሞ ዛሬ በተራዎ የወያኔ መንግሥትን በመታመን ሁሉን ነገር ማድረግ እንደሚችሉ ራስዎትን ያለ ልክ ከፍ ከፍ በማድረግ በጠራራ ፀሐይ ለክብርዎ ሐወልት አቆሙ። "አባ" ሆይ! ሰውስ ሰውን ቢበድል እግዚአብሔር ይፈርድበታል ሰው ግን እግዚአብሔርን ቢበድል ስለ እርሱ የሚለምን ማን ነው? እንግዲህ በጸጸት ይመለሱ እንደሆነ የእስራኤል ቅዱስ እግዚአብሔር የንስሃ ልብ ይስጥዎት።

ውድ አንባቢ ሆይ! የቆመው ሐወልት በሳቸው ትዕዛዝም ይቅረብ በሌሎች በፕሮግራሙ ተስማስተው "አባ" ጳውሎስ በሚሊኒየሙ ማግስት የደመራ በዓል ለማክበር የተገኘውን የዋኅ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ያን እምነት ተከታይ "ጭቃ!" በማለት ለከት የሌለው አፋቸውን ያላቀቁበት ሕዝብ ላይ ያላቸውን ንቀት ብቻ ሳይሆን የገለጹት በምድሪትዋና በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን የወረደ አመለካከትና የልባቸውን ትዕቢት ነው በአደባባይ ይፋ ያደረጉት። "አባ" ጳውሎስ ሐወልት በስማቸውና በምስላቸው የማቆማቸው ምሥጢሩ ይህ ነው እሱም ንቀትና ልክ የሌለው ትዕቢት!!

ውድ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ያን እምነት ተከታዮች! በዛሬ ነገ እዋረዳለሁ በማለት ውድቀቱን ቀን ከሌሊት እየተጠባበቀ የሚገኘውን አእምሮውን ጥሎ በደመ ነፍስ ሕዝብን እንደ እንስሳ እየነዳ የሚገኘው የወያኔ መንግሥት ፍቃድ ሳያገኝ ይህን ሐወልት ይቆማል ብለው ለአንዳፍታ አያስቡ። እኔም ከዚህ እርስዎም ካዛ (እንግዲህ ቀጭን ትዕዛዝ ነው) እናሳያቸው!! ማለታቸው እንጂ "አባ" ጳውሎስ እግዚአብሔር ብቻውን በሚመለክበት ስፍራ ይቅርና በምስላቸውና በስማቸው ሐወልት ሊያቆሙ ድፍን የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዴት አክ ቱፍ ብሎ እንደተፋቸው ሰው ብቻ ሳይሆን ወፍም ታውቃለች።

ሌላው ሐወልቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ተብሎ ሕጋዊነቱ ለማረጋገጥ ደፋ ቀና መባሉን አይድነቀን! "አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማ" እንዳለው ያገሬ ሰው፤ ሰዎች ይቅር ሐወልት ለማቆም የሰው ነፍስ ለመግደልም ቅድሳት መጻህፍትን ተገን አድርገው የሰው ነፍስ አጋድመዋል የንጹሐን ደም አፍስሰዋል እግዚአብሔር ግን በዚህ ሁሉ አይቀደምም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኤልዛቤል የአመጻ ሥራ ሲገልጽ በእንዲህ ዓይነት መልኩ ያስቀምጠዋል "በአክዓብም ስም ደብዳቤ ጻፈች በማኅተሙም አተመችው በከተማው ወደ ነበሩትና ከናቡቴም ጋር ወደ ተቀመጡት ሽማግሌዎችና ከበርቴዎች ደብዳቤውን ላከች በደብዳቤውም ስለ ጾም አዋጅ ንገሩ፥ ናቡቴንም በሕዝቡ ፊት አስቀምጡት ሁለትም ምናምንቴ ሰዎች በፊቱ አስቀምጡና እግዚአብሔርንና ንጉሡን ሰድቦአል ብለው ይመስክሩበት አውጥታችሁም እስኪሞት ድረስ ውገሩት ብላ ጻፈች" ይላል (መጽ. ነገ. ቀዳማዊ 20፥8-10)

ልብ ይበሉ! "ደብዳቤውን ላከች በደብዳቤውም ስለ ጾም አዋጅ ንገሩ" እንዲል የደብዳቤው መልዕክት እንደ እባብ ቀጥቅጣችሁ ግደሉት የሚል ሲሆን ይህ የነፍሰ ገዳይነት ሥራዋም ሕጋዊ ይዘት እንዲኖረው ለማደረግም 1ኛ. በሙሴ ሕግ ቅጣት የሚፈጸመው በሁለት ሰዎች ሲመሰከርበት ሲሆን ይህን ማድረግዋ 2ኛ. ተሳዳቢ በሕጉ መሰረት በድንጋይ ተወግሮ ይሙት እንዲል ፈጸመው የተባለው ወንጀል "ተሳደበ" ማለትዋ 3ኛና ትልቁ የመልዕክቱ ቁልፍ ደግሞ የጾም አዋጅ እንዲነግሩ በማለት የእራኤላውያንን ልብ ለማግኘት ሳይጠራጠሩ ደርጊቱን እንዲፈጽሙ በሚያውቁትና በተለማመዱት ሥርዓት ማዘዝዋ ነበር። የሚያሳዝነው ኤልዛቤል ሁሉን ከሚያውቅ ከልዑል እግዚአብሔር ዓይን ላታመልጥ በሰው ዘንድ ከተጠያቂነት ለማምለጥ ግን ሕግን መጠቃቀስዋ (መጻህፍትን ተገን ማድረግዋ) ሞትዋ እጅግ አሰቃቂ ዓይነት ሞት እንዲሆን አድርጓል።

የጾም አዋጅ ተነገረ ማለት በእስራኤላውያን ባህል ዘንድ ከእግዚአብሔር ፍርድ የተነሣ ጥፋት በሕዝቡ ላይ እንደ መጣና ይህም ጥፋት ሊመለስ የሚችለው ሕዝቡ ራሱን አዋርዶ በጾም ሲቀርብና ኃጢአት የሰራውን ሰው በሞት ሲያስወግዱ ብቻ ነው የሚል

አስተሳሰብ ሕዝቡ እንዲኖረው ኤልዛቤል ይህን አደረገች። ኤልዛቤል "እስኪሞት ድረስ ውገሩት" በማለት የሙሴ ሕግን ጠቅሳ ሕጋዊነት ያለው ደብዳቤ ከጻፈች ይሰራሎት! ተብሎ ሐወልት መቆሙና የቆመው ሐወልት በጎመን ጥቅሶችን መታጀቡ  ምን ይደንቃል? እማይጠቀስ ሆኖ አይደለም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ግን አለ ቦታው መጥቀስና መጠቀም ነፍሰ ገዳይነት ነው!! (ማቴ. 3፥6 ያብብቡ) ከነፍስ ይልቅ ድንጋይ ("የአባ" ጳውሎስ ሐወልት) በልጦ ነው ስለ ሐወልት አስፈላጊነትና አላስፈላጊነት እያልን ጊዜአችን የምንበላው? መጽሐፍ "የተጻፈውን ፍርድ ያደርጉባቸው ዘንድ ለቅዱሳን ሁሉ ይህች ክብር ናት" እንዲል (መዝ. 149፥9) ቁርጡን መናገር ነው እንጂ! ማን ምን ያመጣል በማለት ለክብርዎ ሐወልት አቆሙ አይደል በቃ ሕዝብ ለማደናገር ጥቅስ ማጣቀሱ ምን አመጣው? ሳታማኸን ብላ!! ይህም ለጥቂት ጊዜ ነው።

እግዚአብሔር ያያል ወገኔ! ኤልዛቤል የባልዋን ፍቃድ ለሞምላት ሕግን እንደ ሽፋን ተጠቅማ በንጹሑ ሰው በናቡቴ የፈጸመቺው ግፍ እግዚአብሔር ፍጻሜ እንዳበጀለት ሁሉ የአቶ መለስ አንባገነናዊ ልብ ፍቃድ ለሞሙላት ማለት ይወቀን ዓይነቱ መልዕክት ያለው ሐወልት ላቆሙ ሰውዬም ፍጻሜም በእግዚአብሔር እጅ ነው። "የእግዚአብሔርም ቃል ወደ ቴስብያዊው ወደ ኤልያስ እንዲህ ሲል መጣ ተነሥተህ በሰማርያ የሚኖረውን የእስራኤልን ንጉሥ አክዓብን ትገናኝ ዘንድ ውረድ እነሆ ይወርሰው ዘንድ በወረደበት በናቡቴ የወይን ቦታ ውስጥ አለ አንተም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ገድለህ ወረስኸውን? ("አባ" ሆይ! የወጠጤዎችና የመበለትዋ ምክር ሰምተው ከሕዝብ በዘረፉት ከፍተኛ ገንዘብ መጻህፍት አጣቅሰው ለክብርዎ ሐወልት አቆሙ አይደል?) ብለህ ንገረው ደግሞም እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ውሾች የናቡቴን ደም በላሱበት ስፍራ የአንተን ደም ደግሞ ውሾች ይልሱታል ብለህ ንገረው አክዓብም ኤልያስን ጠላቴ ሆይ አገኘኸኝን? አለው እርሱም እንዲህ ብሎ መለሰለት አግኝቼሃለሁ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ለማድረግ ራስህን ሸጠሃልና ... ደግሞ እግዚአብሔር ስለ ኤልዛቤል በኢይዝራኤል ቅጥር አጠገብ ኤልዛቤልን ውሾች ይበሉአታል ብሎ ተናገረ" (መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 20፥17-20)።

"አባ" ጳውሎስ ሆይ! እንደ እርስዎ ያለ መበለቶች፣ ልጆችና መናፍስት ጠሪዎች በመከሩት ምክር ተነድቶ በእግዚአብሔርና በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ራሱን የሸጠና የተዋረደ ሰው በዘመኔ አላየሁም። በክፋትዎ ታምነዋል የሚያየኝ፣ የሚሞግተኝ የለም የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ያን ምእምን የሚያምነውን (መጽሐፍ ቅዱስን) አያውቅም! ብለዋል ጥበብዎንና እውቀትዎንም አታልሎታል፥ በልቦትም እኔ ነኝ ከእኔም በቀር ሌላ የለምም! ብለዋል ስለዚህ ምክንያት ክፉ ነገር ይመጣቦል ነው የምለው። በንስሃ ይቅርታን በመጠየቅ ይመለሱ! አለዝያ በምዋርትዎም እንዴት እንደሚያርቁት በአጋፋሪዎቻቸውንም እንዴት ከላይ ላይዎ እንደሚያወርዱት አያውቁም! ጉዳት ይወድቅቦታል ያስወግድዎትም ዘንድ አይቻልዎትም የማያውቁትም ጉስቍልና ድንገት ይመጣቦታል። ምናልባትም መጠቀም ይችሉ ወይም ያስደነግጡ እንደ ሆነ፥ ከአስማችዎና ከምንኩሳናዎ ጀምረው ከደከሙበት ከመተችዎ ብዛት ጋር ይቁሙ።

"አባ" ሆይ! መልስዎ አሁንም በእውነት አሻፈረኝ ከሆነ ግን በምክርዎ ብዛት ደክመዋል! አሁንም የሰማይን ከዋክብት የሚቈጥሩ፣ ከዋክብትንም የሚመለከቱ፣ በየመባቻውም የሚመጣውን ነገር የሚናገሩ፣ ቃልትን እንደ አፈር የሚያንከባልሉ፣ ጠመንጃን እንደ ስክርፒቶ ያነገቱ፣ ተነሥተው ከሚመጣቦት ነገር ያድንዎት። እነሆ፥ እንደ እብቅ ይሆናሉ፥ እሳትም ያቃጥላቸዋል ሰውነታቸውንም ከነበልባል ኃይል አያድኑም እርሱም ሰው እንደሚሞቀው ፍም፥ ወይም በፊቱ ሰው እንደሚቀመጥበት እሳት ያለ አይደለም። የደከሙበት ነገሮች እንዲህ ይሆኑቦታል "ከምንኩስና" ዘመንዎትን ጀምሮ ከእርስዎ ጋር ይነግዱ የነበሩ እያንዳንዳቸው ወደ ስፍራቸው ይሄዳሉ፥ የሚያድኖትም የለም።"

በመጨረሻ አርባና አርባ አምስት የሚሆኑትን በጵጵስና ሥም ከፍተኛ ደመዎዝ የሚከፈላቸው (ጥቂቶቹ ዘመነ "ጵጵስናቸው" የወያኔ መንግሥት ዙፋን ላይ እስካለ ድረስ ስለሆነ ነው እንጂ ሁሉም ማለቴ አይደለም) የት ገቡ? ምንስ አሉ? ትናን "አባ" ጳውሎስ ቤ/ያናችን ወደ ዝቅጠት እያመርዋት ነው! ለስህተት ትምህርት እያጋለጥዋት ነው! ... በማለት ከበሮ መቺዎችን ሰብስቦ መለከት ነፍቶ ያስነፋ የነበረው ራሱን እና ጀሌዎቹን በየጋዜጣው ያስተዋወቀ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከቱ "አባ" ተከስተስ ምን አለ? ይደልዎ! ወይስ ውጉዝ ከመ አርዮስ! (ውድ አንባቢ ሆይ! "አንተ" ማለቴ ክብርን የመንሳት አልያም ደግሞ የመዘንጠልም አይደለም "እኛ" በደንብ ስለምንተዋወቅ እንጅ) ወይስ ትዕዛዝ ሰጪው የሽሬው ተወላጅ አቶ አባይ ፀሐዬ አከርካሪያቸው መሰበሩ ይሆን? "አባ" ሆይ! ("አባ" ተከስተን) እስቲ ልጠይቅህ ከምርጫ 2002 ወዲህ ኳስዋ ጠቅልላ በአድዋ ልጆች ተወላጆች እጅ ወደቀች እንዴ? ቢሆን ነው እንጂ ይህ አጋጣሚ ለአንተና ለሰፈርህ ልጆች ተፈልጎ የማይገኝ ወርቃማ ዕድል እንደሆነ (ጥሎ ለማለፍ ማለት ነው) አንተም እኔም አንስተውም። (<u>እንግዲህ ውድ አንባቢ ከተለመደው ፀባዬን ወጣ በማለት እስከ ሰፈር ድረስ የዘለቅኩት ሌላ ነገር ውስጥ ለመግባት ሳይሆን የሚያብለጨልጭ ሁሉ ወርቅ እንዳይደለ በቤ/ያን ሥም የሚጮክ ጩኸት ሁሉ ይመርመር ማለቴ ነው!! ከታልቅ ይቅርታ!</u>) የጠያቂ ያለህ! ጥያቄዬን አድርሱልኝ!!

ጥበብ በዚህ አለ! አዚምና ድንዛዜ የሚረጩ የትውልድ አሽክላዎችና ለምድራችን እርግማን የሆኑ ቃል በቃል ዘማዊት ማለት ብቻ የቀራቸው ብሔራዊት ጥንታዊት ታሪካዊት ጦር-ሰራዊት እያሉ የምእመናን ልብ በማዋለል ከፍተኛ ንዋይና ሀብተ ንብረት ያግበሰበሱ ሕጋዊያን ሽፋቱ "...ዊት" ለመለያቸው ደቂቀ-አኪጦፌል የሰይጣን ማኅበር "ማኅበረ-ቅዱሳን" እንኳን ድምጻቸው መጥፋቱ ሳይሆን ተቆርቋሪነታቸውና ትውፊት ጠባቂነታቸው በተግባር ቢያሳዩ ነበር የሚደንቀኝ። አይ የአገሬ ሰው እስከ መቼ ይሆን በድንግዝግዝ ህይወት ውስጥ የምትመላለሰው? ሌላው ይቅር ዛሬ እንኳን ንቃ!! እንግዲህ የሚያስጮኸን ይህ ነው በዘመናት ሁሉ ወቅትንና ሰዓታትን እየጠበቁ በበረከት ፈንታ እርግማንን ያዘነቡብን ዛሬ እንደ ማልያ መለያችን አድርገን የያዝናቸው ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ የሌላቸው "የእምነት መገለጫዎቻችን" ሾልኮው የተጋጉግን በእንዲህ ዓይነት መልኩ (በቀላሉ) ነበር። የዛሬዋ "የአባ" ሐወልት ስትውል ስታድር ከ አንድ ትውልድ በኋላ ደግሞ በታቦት ፈንታ ትመለካለች። ንቃ! የማታቀውን ነገር ለማወቅ ጉጉት ይንሩርህ! ወደ ጣልከው የህይወት መውጪያና መግቢያ ቁልፍ ወደ ያዘ መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ፊትህን አዙር በዚያም ለጥያቄዎችህን መልስ ታገኛለህ።

ለማንኛውም፥

- በእርሱ የሚያምን ሁሉ ለዘልዓለም ሕይወት እንዲኖረው፤
- ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፤
- በእርሱ ባለጸጎች እንድንሆን፤
- ኃጢአትን በሥጋ ሊኮንን፤
- የጥል ግድግዳን በሥጋው ሊያፈርስ፤
- በሥጋ ሰውነቱ በሞቱ ሊያስታርቀን፤
- ከሕግ እርግማን ሊዋጀን፤
- እንዲሁም ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርበን ሰማያዊ ዝፋኑን ትቶ ደሙን አፍስሶ ሕይወትን የሰጠን ጅምር የሌለው ዘመን- ጊዜ ሳይቀመር ሳይተመን- ገና ሳይለይ ምኑ ከምን-ቃል የነበረ በሰማይ የአማልክት አምላክ፤ የጌቶች ጌታ፤ የነገሥታት ንጉሥ፤ የገዢዎች ገዢ ብርሃንን እንደ ልብስ የለበሰ በክብር በአብ ቀኝ ያለው ከሙታን መካከል በኩራት ሆኖ የተነሳ ክብር፤ ምሥጋና፤ ውዳሴ፤ ስግደትና አምልኮ የተገባውና አምሳያ የሌለው ከይሁዳ ነገድ የሆነ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ እንኳን ሐወልት አቁሙልኝ አላለም!! ድንቄም ክርስቲያን!

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ያን ተከታዮች (ምዕመናን) ሆይ! ብርሃን የሚመስል ጨለማ፤ ትክክል የሚመስል የጥፋት መንገድ፤ እውነት የሚመስል ውሸት፤ ሕጋዊ የሚመስል ሕገወጥ፤ ቅዱስ የሚመስል እርኩስ፤ መልአክ የሚመስል ሰይጣን፤ አምላክ የሚመስል ጣዖት ነውና ሁሌ እርግብ ልሁን ብትል ዘንዶ እንዳይውጥህ ለራስህ ደህንነት ስትል ተጠንቀቅ!! ንቃ!!

- ሳዖል ባለመጠንቀቁ (ነህዝላልነቱ) ንጉሥ እንዳይሆን እንደ ተናቀ (1ኛ ሳሙኤል 15፥26)
- ዖዛ ባለመጠንቀቁ (እኔነት፤ ትዕቢት) በእግዚአብሔር ተቀስፎ እንደ ሞተ (2ኛ ሳሙ. 6፥6-8)
- አካን ባለመጠንቀቁ (ሌብነት) በድንጋይ ተወግሮ እንደ ሞተ (ኢያሱ 7፥25)
- ይሁዳም ባለመጠንቀቁ (ከህደቱ፤ ስስቱ፤ ሌብነቱ) ክርስቶስን እንደ ሸጠ (ማር. 14፥10-11)
- እንዲሁም ናዳብና አብድዩም በድፍረት የራሳቸው እሳት በእግዚአብሔር መሰዊያ ላይ ሲያቀርቡ እግዚአብሔር ተቆጥቶ እንደ ቀሰፋቸው። “የአባ” ጳውሎስ ዓይን ያወጣ እኔነት፤ ትዕቢት፤ ክህደት፤ ሌብነትና ነህዝላልነት 5ኛ የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ያን “ፓትሪያሪክ” ተብለው መጠራት ብቻ ሳይሆን በእነዚህ ከባድና ተደራራቢ ወንጀሎች፤ ነውሮችና ክፉ ድርጊት /ኢ-ክርስትያናዊ ምግባር/ ተጠያቂ ናቸው።

ጥብቅ ማሳሰቢ ለአንባቢያን፥ ሐወልትን ስለ ማቆም በማስመልከት የጻፍኳቸው ጽህፎች በመንፈሳዊነት ሥም በቤተ-ክርስትያን ቅጽር ግቢ ስለሚታነጹ አልኩ እንጅ በውጭ ስለሚቆሙም ሆነ በመቃብር ሥፍራ ስለሚታነጽ ሐወልቶችን አይመለከትም።

**በጌታ ደስታዬ ሙሉ ነው**
**ግዞተኛው ዲያቆን ሙሉጌታ ወልደገብርኤል ነኝ**
**ከሀገረ አሜሪካ!**